
በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት
# የሥራ ሁኔታን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
# የቀረበ አጠቃላይ መግለጫ



አዲስ አበባ
ጥር 20 ቀን 1989

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት
# የሥራ ሁኔታን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
# የቀረበ አጠቃላይ መግለጫ

አዲስ አበባ

ጥር 20 ቀን 1989

# ማ ዉ ጫ


ገጽ

1. መግቢያ 1

2. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አመሠራረትና ዕድገት፣ 1

3. መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው አብይ ተግባሮች፣ 2

4. የመሥሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር፣ 4

5. መሥሪያ ቤቱ ያከናወናቸው ዋና ዋና ጥናቶችና ቆጠራዎች፣ 6

5.1 የተከናወኑ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ ዲሞግራፊያዊ ጥናቶች፣ 7

5.2 የተከናወኑ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች፣ 8

6. በ1989 በጀት ዓመት በመካሄድ ላይ ያሉ ጥናቶች 9

6.1 የተቀናጀ ሀገር አቀፍ የቤተሰብ ጥናት መርሐ-ግብር 10

6.2 በ1989 በጀት ዓመት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታቲስቲክስ በተመለከተ በመካሄድ ላይ ስላሉ ጥናቶች የተሰጠ ማብራሪያ 11

7. የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ 20

8. የመ/ቤቱ የፋይናንስ አጠቃቀም ሁኔታ፣ 21

9. በልምድ ልውውጥ የስታቲስቲክስ ሥራን ለማሻሻል የተከናወኑ ተግባራት፣ 23

10. የመሥሪያ ቤቱ ሥራዎችን ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸዉ መሣሪያዎች ሁኔታ፣ 23

11. ያጋጠሙ ችግሮች፣ 24

12. የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የወደፊት የሥራ እቅድ፣ 25

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት

## የሥራ ሁኔታን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

## የቀረበ አጠቃላይ መግለጫ

1. **መግቢያ**

የአሁኑ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣ የጠቅላይ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ተብሎ ከተቋቋመበት ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ ያሣየዉን የአደረጃጀት ለዉጦች፣ ያከናወናቸዉን ተናቶች፣ በሰዉ ኃይል፣ በበጀትና በልዩ ልዩ መሣሪያዎች ረገድ ያሣየዉን ዕድገት፣ እንደዚሁም የስታቲስቲክስ አሠራርን ለማሻሻል የተደረገዉን ጥረትና በሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ከዚያም የመሥሪያ ቤቱ የወደፊት እቅድ የሚመለከት አጭር ዘገባ እንደሚከተለው ቀርቧል።

2. **የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አመሠራረትና ዕድገት**

በሀገራችን የስታቲስቲክስ ሥራ እንደማንኛውም መደበኛ ሥራ ተቀጥር ተግባራዊ መሆን የጀመረው በ1952 ዓ.ም ነበር። ለዚህም መነሻ የሆነው በ1952 ዓ.ም መግቢያ ላይ የመጀመሪያው የአፍሪካ ስታቲስቲሺያኖች ጉባዔ በአዲስ አበባ ተደርጎ እያንዳንዱ በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አባል ሀገሮች የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲያደርጉ በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ነው።

በዚህ መንስኤ የተጀመረው የስታቲስቲክስ ተግባር ይካሄድ የነበረው የንግድ፣ የኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ተቋቁሞ በነበረው መ/ቤት ስር ነበር። ይኸው ጅምር አድጎ በ1955 ዓ.ም የስታቲስቲክስ መ/ቤት እራሱን የቻለ ድርጅታዊ አቋም ተሰጥቶት በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሥር ተዋቅር እስከ 1958 ዓ.ም መጀመሪያ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር በኋላም የፕላን ኮሚሽን ለሚባለው መሥሪያ ቤት ተጠሪ ሆኖ እንዲሠራ ተደርጓል።

በ1964 ዓ.ም በወጣ አዋጅ ቁጥር 303/1964 መሠረት ደግሞ መሥሪያ ቤቱ የሕግ ሰውነት አግኝቶ ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ ተጠሪነቱ እስከ 1971 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በጊዜው ለነበረው የፕላን ኮሚሽን ከዚያም ከ1971 እስከ 1979 ዓ.ም

ድረስ ደግሞ ለብሄራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ፣ በኋላም ለማዕከላዊ ፕላን ብሄራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ተጠሪ በመሆን ሥራውን ሲያካሄድ ቆይቷል።

የመሥሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመምጣቱ ድርጅታዊ አወቃቀሩን ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መሥሪያ ቤቱ እንደገና ሊደራጅ ስለሚችልበት ሁኔታ የመዋቅር ጥናት ተደርጎ "የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን" በመባል ከመጋቢት 9 ቀን 1981 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል። ተጠሪነቱም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የነበረ ሲሆን ከ1988 ዓ.ም ጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ ደግሞ ተጠሪነቱ ለኢካኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር እንዲሆን ተወስኖአል።

## 3. <u>መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው አበይት ተግባሮች</u>

የአንድን ሀገር ሕዝብ/ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ከፍ ለማድረግ ለሚቀየሱ የማሕበራዊና የኢኮኖሚያዊ ልማት ዕቅዶች ዝግጅት፣ እንዲሁም የተዘጋጁት ዕቅዶች በተግባር ላይ ሲዉሉ ዉጤቶችን ለመከታተል፣ ለመገምገምና የተለያዩ ጥናቶችን/ምርምሮችን ለማካሄድ በሥርዓት የተሰበሰቡና የተቀነባበሩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች መነሻ/መሠረት ሆነዉ ያገለግላሉ። ይህን ለማድረግና በሥራም ለመተርጎም በየዘርፉ የመረጃዎች ተሟልቶ መገኘት አስፈላጊ ነው። የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ለመረጃ ሀብት ክምችት መዳበር ከፍተኛ ጥረት ያደረገና በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው ዓቢይ ተግባራትም እንደዚሁ እያደጉና እየሰፉ መጥተዋል። መሥሪያ ቤቱ ከሚያከናዉናቸው ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸዉ።

3.1 በስታቲስቲክስ ጉዳይ ሁሉ በጠቅላላዉ ለመንግሥት ምክር መስጠት፣

3.2 የስታቲስቲክስ መረጃዎች መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን፣ በጽሁፍ ማዉጣትና ማሰራጨት፣

3.3 ስለሀገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መረጃዎች ማዕከል በመሆን ማገልገል፣

3.4 ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ የመንግሥት መመሪያዎችና ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸዉን መቆጣጠር፣ የስታቲስቲክስ ተግባራት በሚከናወኑበት ጊዜ የወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች የሚከተሉ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፣

3.5 ለመንግሥት ስታቲስቲካዊ አገልግሎት የሚዉሉ የረጅምና የአጭር ጊዜ የስታቲስቲክስ ፕላኖች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ ሲፈቀድ በሥራ ላይ መዋላቸዉን ማረጋገጥ፣

3.6 የመንግሥት መ/ቤቶችን የስታቲስቲክስ ሥራዎች መምራትና ማስተባበር፣ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴያቸዉን የሚያሳዩ የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝ እንዲቋቋም ማድረግ፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠትና ሥራዉን መቆጣጠር፣

3.7 ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከአስተዳደር መዛግብት የሚገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ማቅረብ፣

3.8 ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ የመንግሥት መ/ቤት ጋር በመተባበር የሕዝብና ቤት ቆጠራና ሌሎች ቆጠራዎች ማካሄድ፣ እንዲሁም የስታቲስቲክስ ጥናቶችና ምርምሮችን ማዘጋጀትና መምራት፣

3.9 ለጠቅላላዉ የመንግሥት የስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚዉል የስታቲስቲክስ ትርጉምና አመዳደብ ማዉጣትና መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

3.10 የመንግሥት መ/ቤቶች የስታቲስቲክስ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን ሥርዓት መወሰንና መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

3.11 የሚሠራባቸዉን የስታቲስቲክስ ሥራዎች ዘዴ በየጊዜዉ በመገምገም ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ጥረት ማድረግና መመሪያ መስጠት፣

3.12 በስታቲስቲክስ ዘገባዎች ተጠቃሚ የሆኑ መ/ቤቶችንና የሌሎችን ክፍሎች ፍላጎት ለማርካት እንዲቻል በባለሥልጣኑና በተጠቃሚዎች መሃከል የቅርብ ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር ሴሚናሮችና ስብሰባዎች በማካሄድ አስፈላጊዉን ሁሉ ማድረግ፣

3.13 ከሌሎች አገሮች የስታቲስቲክስ መ/ቤቶችና የኢንተርናሽናል ድርጅቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠርና በኢንተርናሽናል የስታቲስቲክስ ፕሮግራሞች ተካፋይ ለመሆን እንዲቻል አስፈላጊዉን ሁሉ ማድረግ፣

3.14 አግባብ ካላቸዉ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመስማማትና በመተባበር እንዲሁም ዉክልና በመስጠት የስታቲስቲክስ ሥራዎችንና ፕሮግራሞችን ማከናወን፣

3.15 ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የኮሚሽን ጽ/ቤት ሆኖ ማገልገልና ተግባሩን ማከናወን፣

3.16 ከመንግሥት የሚተላለፉ ሌሎች ሥራዎች ማከናወን ናቸዉ።

4. <u>የመሥሪያ ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር</u>

መሥሪያ ቤቱ በአንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ በሁለት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆች ፣ በአንድ የሀዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ኃላፊ እንደዚሁም ከላይ በተጠቀሱት ኃላፊዎች የሚመሩ በስምንት መምሪያዎች፣ በአምስት የማዕከሉ ማስተባበሪያዎችና በስድስት አገልግሎቶች ተዋቅሮአል። በተጨማሪም 15 የስታቲስቲክስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ዋናው መሥሪያ ቤት በሚያወጣው ዕቅድና የሥራ ፕሮግራምን በማስፈጸም ላይ ይገኛሉ። የድርጅታዊ መዋቅሩም ዝርዝር እንደሚከተለዉ ነዉ፣

ሀ. ዋና ሥራ አስኪያጅ

ለ. የኢኮኖሚና የሶሻል ስታቲስቲክስ ማስተባበሪያ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ይህም ማስተባበሪያ የሚከተሉት አምስት መምሪያዎች አሉት፣

- የማሕበራዊና የቤቶች ጉዳይ ስታቲስቲክስ መምሪያ፣

- የግብርና ስታቲስቲክስ መምሪያ፣

- የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ መምሪያ፣

- የንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ቱሪዝም ስታቲስቲክስ መምሪያ፣ እና

- የብሄራዊ አካዉንትስ፣ የዋጋና የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ መምሪያ፣ ናቸዉ።

ሐ. የአጠቃላይ ስታቲስቲክስ ማስተባበሪያ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ይህም ማስተባበሪያ የሚከተሉት ሶስት መምሪያዎች አሉት፣

- የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶችና የመስክ ሥራ ክንዉን መምሪያ፣

- የሚቶዶሎጂ መምሪያ፣ እና

- የመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ፣ ናቸዉ።

መ. የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል ኃላፊ፣ ማዕከሉም የሚከተሉት አምስት የጥናትና የምርምር ማስተባበሪያዎች አሉት፣

- የሕዝብ ጉዳይ ፖሊሲ ጥናት፣ ምርምርና ግምገማ ማስተባበሪያ፣

- የሥነ ሕዝብ ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር ማስተባበሪያ፣

- የሻይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባና ሥርዓት ጥናትና ምርምር ማስተባበሪያ፣

- የሰዉ ኃይል፣ ደመወዝና የምንዳ ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር ማስተባበሪያ፣ እና

- የሕዝብ ፍልሰት፣ አሠፋፈርና የመከተም ስታቲስቲክስ ጥናትና ምርምር ማስተባበሪያ፣ ናቸዉ።

ሠ. በተጨማሪም የባለሥልጣኑ መ/ቤት መዋቅር የሚከተሉት ስድስት አገልግሎት አካላትም አሉት፣

- የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት፣
- የፐሎንና ፕሮግራም አገልግሎት፣
- የኦዲት አገልግሎት፣
- የሥራ አመራርና ማሰልጠኛ አገልግሎት፣
- የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት፣ እና
- የሕግ አገልግሎት፣ ናቸዉ።

5. <u>መሥሪያ ቤቱ ያከናወናቸው ዋና ዋና ጥናቶችና ቆጠራዎች</u>

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሥራዉን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአገር አቀፍ ደረጃ የማሕበራዊና የኤኮኖሚ ልማት ዕቅድዶችን ለማዘጋጀት እንዲሁም የዕቅዶችን ተግባራዊ መሆንና ዉጤታቸዉንም ለመከታተል መሠረት የሚሆኑ በርካታ የማሕበሪዊ፣ የኢኮኖሚና የዲሞግራፊ ስታቲስቲክስ ጥናቶች አካሂዷል። በተለይም ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በገጠር የተቀናጀ የሰርቬይ ፕሮግራም ተቋቁሞ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥናቶች እየተካሄዱ ሲሆን እንደዚሁም ሁለት ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች አካሂዷል።

5.1 <u>የተከናወኑ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊያዊ ጥናቶች</u>

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ያካሄዳቸዉ ጥናቶች በርካታ ሲሆኑ ከ1981-1988 ባሉት ዓመታት ካካሄዳቸዉ ጥናቶች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

ሀ) <u>በቋሚነት በመደበኛ በጀት የሚካሄዱ ጥናቶች</u>

- ዓመታዊ የማምረቻ እንዱስትሪዎች ጥናት፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት፣ (ዓመታዊ)
- የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣ /በየወሩ/ እና
- በተመረጡ 23 ከተሞች የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፣ /በየወሩ/ ናቸዉ።

ለ) <u>በካፒታል በጀት የሚካሄዱ ጥናቶች</u>

ከነዚህ በተጨማሪ ፕሮጀክት ዶክሜንት እየተዘጋጀላቸው በዕቅድ የተያዙና የተደገፉ ልዩ ልዩ ጥናቶች መሥሪያ ቤቱ አካሂዷል። እነዚህም

- የግብርና ናሙና ጥናት፣ (ዓመታዊ)
- የሰብል ትንበያ ጥናት፣ (ዓመታዊ)
- የቤተሰብ ገቢ፣ የፍጆታና ወጪ ጥናት በገጠርና በከተማ፣
- የኢኮኖሚና ማኀበራዊ ደህንነት ጥናት በገጠርና በከተማ፣ (ለተከታታይ አምስት ዓመታት)
- የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠር፣
- የወሊድና የቤተሰብ ሁኔታ ጥናት በአዲስ አበባ፣
- የጤናና የአመጋገብ ጥናት፣
- የአካል ጉዳተኞች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥናት፣ እና
- የምግብ አቅርቦት ዋስትና (Food Security Survey)፣ (በገጠር) ናቸዉ።

## 5.2 የተከናወኑ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የብሄራዊ ሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደዉ በ1976 ነበር። ይህንን ቆጠራ ለማስፈጸም እንዲረዳ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋም በማስፈለጉ ኮሚሽኑን ለማቋቋም አዋጅ ቁጥር 252/1976 ወጥቷል። በዚህ አዋጅ መሠረት በሀገሪቱ የመጀመሪያዉ ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በ1976 ተካሂዷል። የሕዝብና ቤት ቆጠራም በየአሥር ዓመቱ የሚካሄድ ፕሮጀክት እንደመሆኑ መጠን በጥቅምት ወር 1985 በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 32/1985 መሠረት ሁለተኛው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በጥቅምት ወር 1987 ዓ.ም ተካሂዷል። የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤትም የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በመሆን የቆጠራዉን ተግባር አከናዉኖአል።

በጥቅምት ወር 1987 የተካሄደዉን አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት በብቃት ለመወጣት ከጥቅምት ወር 1985 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ዝርዝሩ ስለፕሮጀክቱ በሚቀርበዉ ሪፖርት ይሰጣል።

## 6. በ1989 በጀት ዓመት በመካሄድ ላይ ያሉ ጥናቶች

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በዚህ በጀት ዓመትም በርካታ ጥናቶችን ለማካሄድ አቅዶ ተግባራዊ በመድረግ ላይ ነዉ። በጥቅምት ወር 1987 በተካሄደዉ የአገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰበዉን መረጃ በኮምፒዉተር የማቀነባበሩና የሪፖርት ዝግጅቱም ተግባር በዚህ በጀት ዓመትም እንደቀጠለ ሲሆን በዛሬዉ ዕለት ስለቆጠራዉ ፕሮጀክት በሚቀርበዉ ሪፖርት ዝርዝሩ ይሰጣል። በመሆኑም በዚህ በጀት ዓመት በተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የኢኮኖሚና የማሕበራዊ መረጃዎች ከምችትን በስፋትና በጥልቀት ለመሰብሰብ የባለሥልጣኑ መ/ቤት በሚያደርገዉ ጥረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስራ ሁለት ዓይነት ጥናቶችን እያካሄደ ነዉ።

i. ሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /ገጠር/

ii. የግብርና ናሙና ጥናት /ገጠር/

iii. የዋጋ ጥናት /በከተማና በገጠር/

iv. መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘረፍ

v. አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች

vi. የአከፋፋይና ንግድ አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅት ጥናት

vii. የጎጆ/የዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

viii. ዓመታዊ ትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

ix. የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ደህንነት ጥናት

x. የኮንስትራክሽን ጥናት

xi የእንሰት ጥናት

xii. የዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሄት ዝግጅት

ከነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ በ1988 በጀት ዓመት በተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸዉ ተጠናቆ የማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት ተግባራቱ ወደ 1989 በጀት የተሸጋገሩ ሶስት የተለያዩ ጥናቶች ይጠናቀቃሉ። እነዚህም፣

ሀ) የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት (በገጠርና በከተማ)፣

ለ) የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ደህንነት ጥናት (በገጠርና በከተማ)፣ እና

ሐ) የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናት (በገጠርና በከተማ)፣ ናቸዉ።

## 6.1 <u>የተቀናጀ ሀገር አቀፍ የቤተሰብ ጥናት መርሐ-ግብር</u>

ለተለያዩ የዕድገት ዕቅዶችን ለመንደፍና መርሐ-ግብሮችን መከታተያና መገምገሚያ የሚሆን ያልተቋረጠ የማሕበራዊ፣ የኢኮኖሚና የስነሕዝብ መረጃ አቅርቦት ሊያስገኝ የሚችል ሀገር አቀፍ የስታቲስቲክስ መርሐ-ግብር ያስፈልጋል። በመሆኑም በተለያዩ መስኮች ያለዉን የመረጃ እጥረት በመገንዘብ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሀገር አቀፍ የተቀናጀ የቤተሰብ ጥናት መርሐ-ግብርን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካል በሆኑት FAO, UNDP እና UNICEF እጋዥነት በ1972 ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ።

በኢትዮጵያ ተግባራዊ በመሆን ላይ ያለዉ ሀገር አቀፍ የተቀናጀ የቤተሰብ መርሐ-ግብር ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛዉና በስፋት ያለማቋረጥ

የሚከናወነዉ የገጠር የተቀናጀ የቤተሰብ ጥናቶች መርሐ-ግብር ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ የከተማ የተቀናጀ የቤተሰብ ጥናቶች መርሐ-ግብር ነዉ። የጥናቱ መርሐ-ግብር መነሻ ያደረገዉም ቤተሰብን ነዉ። የዚህ መርሐ-ግብር አፈጻጸም የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት።

ሀ. በመርሐ-ግብሩ የተካተቱ የተለያዩ የገጠርና የከተማ ማሕበራዊ፣ የኢኮኖሚና ስነሕዝባዊ ጥናቶች የሚሸፍኑዋቸዉ የናሙና አካባቢዎች /ለምሳሌ ገበሬ ማሕበሮች፣ የከተማ ቀበሌዎች/ ለተወሰኑ ዓመታት በቋሚነት የሚቆዩ ይሆናሉ። በተጨማሪም ለጥናቶች አፈጻጸም ማለትም ለያንዳንዱ ጥናት ከሚመለከታቸዉ ቤተሰቦች መረጃ የመሰብሰቡ ተግባር የሚከናወነዉ በተወሰነ የጥናት ሥፍራ (በከተማ/በገጠር ቀበሌዎች) በቋሚነት በሚመደቡ የመስክ ሠራተኞች ናቸዉ።

ለ. በሀገሪቱ ያለዉን የተቀናጀ የመረጃ ክምችት ወጥ ባለዉ መንገድ የማስፋፋትና የማዳበር ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል። በመርሐ-ግብሩ የሚሰበሰቡ የተለያዩ መስኮችን የሚያንጸባርቁ መረጃዎችን የተቀናጀ የመረጃ ቅንብር በርካታ ግልጋሎቶች የሚሰጡ ዉጤቶች ማስገኘት ይቻላል።

በ1973 የተጀመረዉ የተቀናጀ የቤተሰብ ጥናት መርሐ-ግብር ከጊዜ ወደ ጊዜ የስፋትና የጥልቀት እድገት እያገኘ በአሁኑ ጊዜ በገጠር 720 ገበሬ ማሕበሮችን በከተማ ደግሞ 447 ቀበሌዎችን በመሸፈን የተለያዩ የማሕበራዊ፣ የኢኮኖሚና የስነ ሕዝብ ጥናቶችን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በማካሄድ ላይ ይገኛል። በመሆኑም በ1989 በዚህ መርሐ-ግብር የሚካሄዱትን ጥናቶች በተመለከተ አጠር ያለ መግለጫ ከዚህ በማስከተል ይቀርባል።

## 6.2 በ1989 በጀት ዓመት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ በመዝረድ ላይ ስላሉ ጥናቶች የተሰጠ ማብራሪያ

### 6.2.1 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሀገር ውስጥ ለምግብ ፍጆታ የሚውል የሰብል ምርት በቂና ከበቂ በላይ እንደሚሆን ወይም ዕጥረት ሊኖር እንደሚችል በቅድሚያ በመገመት በሰብል ምርት ወደፊት ሊደርስ የሚችለውን ዕጥረት ወይም ትርፍ ለመገምገምና ወደ አገር ለማስገባትም ሆነ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ ለመላክ (Import-Export) ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማቅረብ ነው።

የዚህ ጥናት መረጃ በየዓመቱ ከመስከረም 1 እስከ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ በሳይንሳዊ ዘዴ በናሙና ከተመረጡ የገበሬ ቤተሰቦች የሚሰበሰብ ነው። ለዚህም ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ተግባር ተፈጸሞ መረጃዎቹ ከመስክ ወደ ዋናው መ/ቤት ተልከው አስፈላጊው የእርማትና የኮድ አሠጣጥ ተግባር እንደተከናወነ መረጃዎቹን በኮምፒዩተር አቀነባብሮና ተንትኖ የጥናቱን ውጤት በኅዳር ወር መጨረሻ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ አድርጓል።

### 6.2.2 የግብርና ናሙና ጥናት

ሀገሪቱ በየዓመቱ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለምታዘጋጀው የአጭርና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅድ የሚረዳ መረጃ ለማስገኘት የሚካሄደው የግብርና ናሙና ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

ሀ. በሀገሪቱ የተመረተውን አጠቃላይ የሰብል ምርት ለማወቅ፣ በክልሎችና በዞን ደረጃ ያለውን የምርት ሁኔታ ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

ለ. ከአንድ ሄክታር ላይ የሚገኘው ምርት ምን ያህል እንደሆነና በክልሎችና በዞኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚረዳ መረጃ ለማግኘት፣

ሐ. ከዓመት ወደ ዓመት ያለውን የምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት በመኸርና በበልግ ወቅት በመለየት በሰብል ዓይነት የታየውን ለውጥ ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

መ. የእርሻ ሥራን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ጥቅም ላይ የዋለ ማደበሪያ፣ ምርጥ ዘርና የፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነት እንዲሁም የመስኖ አጠቃቀም ወዘተ... ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣

ሠ. በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ማለትም በሰብል ስለተያዘ መሬት፣ እጻሪ መሬት ፣ በግጦሽ የተያዘ መሬት፣ በደን የተሸፈነ መሬት ወዘተ... የሚያሳይ መረጃ ለማግኘት፣

ረ. በአገሪቱ ያሉትን የቤት እንስሳትን በተመለከተ፡-

- ብዛታቸውን በዓይነት፣ በዕድሜና በጾታ
- ብዛታቸውን በሚሰጡት ጥቅም አኳያ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፣

ከግብርና ናሙና ጥናት ከሚሰበሰቡ መረጃዎች በየዓመቱ የተለያዩ ይዘት ያላቸው ሪፖርቶች በ5 ጥራዞች ተዘጋጅተው ለተጠቃዊዎች ይሠራጫሉ:: እነዚህም፡-

Vol.1 Area and Production in Meher Season for Private Holdings

Vol.2 Livestock Poultry and Beehives Population

Vol.3 Report on Agricultural Practices

Vol.4 Report on Land Utilization

Vol.5 Area and Production for Belg Season, Private Holdings

በያዝነው በጀት ዓመታም ይኸው ጥናት እየተካሄደ ሲሆን መኸር ወቅትን በተመለከተ መረጃው ከመስከረም እስከ የካቲት ወር ድረስ ይሰበሰባል:: እንዲሁም የበግል ወቅት መረጃም በግንቦት ወር ይሰበሰባል:: የዓመቱ የግብርና ጥናት አካል የሆነው የሰብል ምርት ግብአቶችን የሚያሳይ መረጃ የመሰብሰብ ተግባር ተጠናቅቆ በአሁኑ ወቅት በዋናው መ/ቤት መረጃው በኮምፒውተር እየተቀነባበረ ነው:: የቤት እንስሳት፣ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛትን የሚያሳይ ጥናት በየዓመቱ ከታህሣሥ 24 (እ.አ.አ. January 1) ጀምሮ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ ቆጠራው ስለሚካሄድ የዚህ ጥናት መረጃ በአሁኑ ወቅት ተሰብስቦ ወደ ዋናው መ/ቤት በመምጣት ላይ ይገኛል:: በአጠቃላይ በዘንድሮው የግብርና ናሙና ጥናት የሚሰበሰቡት መረጃዎች ላይ አስፈላጊው የእርማትና ኮድ አሠጣጥ ተግባር ተከናውኖ ተቀነባብሮና ተተንትኖ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች በግንቦት ወር እንደሚሰራጭ ይጠበቃል::

የመኸር ወቅት ሰብል ምርትን በተመለከተ መረጃው የሚሰበሰበው በሁሉም አካባቢ ያሉ ሰብሎች በሙሉ እስኪሚታጨዱ ድረስ ስለሚጠበቅ መረጃው በአሁኑ ወቅት በመስክ ላይ እየተሰበሰበ ነው። መረጃው ተሰብስቦና ተጠናቆ ወደ ዋናው መ/ቤት እንደመጣም ተቀነባብሮና ተተንትኖ እስከ ሰኔ ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚዎች ይሰራጫል።

### 6.2.3 የዋጋ ጥናት - በከተማና በገጠር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በከተማ የዋጋ ጥናት ማካሄድ የጀመረው በአዲስ አበባ ከ1957 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን በገጠር ደግሞ ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። በከተማ የተካሄደው የችርቻሮና የጅምላ ዋጋ ጥናቶች ሲሆኑ በገጠር ግን የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናቶች ናቸው። ሆኖም ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ መንግሥት የጅምላ ንግድን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠሩ ምክንያት የጅምላ ዋጋ ጥናት የተቋረጠ ሲሆን የነፃው ገበያ ሥርዓት እየተስፋፋ ባለበት በአሁኑ ወቅት የጅምላ ዋጋ ጥናት መቀጠል አስፈላጊነቱ እየጎላ መጥቷል። መ/ቤቱም ጥናቱን በቅርቡ ለመጀመር እያቀደ ነው። የዋጋ ጥናት ዓላማዎችና ጥቅሞች በርካታ ሲሆኑ ከእነዚህ መሃል በዋናነት የሚጠቀሰው በየጊዜው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያሳየውን ለውጥ ለመገንዘብ ብሎም ፖሊሲ አመንጪዎችና ተመራማሪዎች የምርት ዋጋና ሥርጭቱ የሚያሳየውን አዝማሚያ በማጤን መወሰድ የሚገባውን እርምጃ ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት ነው።

የዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰቡ ሂደት በተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም ውስጥ የተካተተ በመሆኑ በየወሩ በገጠርና በከተማ የዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። በነዚህ ጥናቶች አማካይነትም የችርቻሮና የአምራች ዋጋዎች መረጃዎች ይሰበሰባሉ። ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ በየወሩ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶችን /በአገር አቀፍ፣ በገጠርና በከተማ ደረጃ/ መ/ቤቱ ያዘጋጃል።

የችርቻሮ እንዴክስ ማለት ሸማቾች ለተወሰኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የከፈሉትን አማካይ የዋጋ ለውጥ ለማሳየት የሚያገለግል አሀዝ ወይም በሕብረተሰቡ ላይ የሚታየውን የዋጋ ግሽበት በሙቶኛ ለመለካት የሚያስችል አሀዝ ነው። ይህንን የችርቻሮ ዋጋ እንዴክስ ለማዘጋጀት የባለሥልጣኑ መ/ቤት በመላ ሀገሪቱ በናሙና በተመረጡ ቦታዎች በ1988 በጀት ዓመት ያካሄደውን የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን የአገር አቀፍ የገጠርና የከተማ የዋጋ እንዴክሶች እያዘጋጀ በያዝነው በጀት ዓመት ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ጀምሯል።

በየወሩ የሚሰበሰቡት የዋጋ መረጃዎች በዋናው መ/ቤት የኤዲቲንግና የኮዲንግ ሥራ ይከናወናል። ከዚያም መረጃዎቹ በኮምፒዩተር ተቀነባብረው ለመረጃ ተጠቃሚዎች ወቅታቸውን ጠብቀው የጥናቱ ሪፖርቶች ተዘጋጅቶና ታትመው ለተጠቃሚዎች ይሠራጫሉ።

በያዝነው በጀት ዓመት ውስጥ አራት ድርጅት ነክ የሆኑ ጥናቶች ማለትም መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች እንዲሁም የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በክልል ዋና ከተሞችና በሌሎች የአገሪቱ አበይት ከተሞች ውስጥ በቅደም ተከተል እየተካሄዱ ይገኛሉ::

<u>መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ</u> የሚባለው በግል ወይም በቤተሰብ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት /የሥራ መስክ/ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ባለቤቶች ሠራተኛ ሳይቀጥሩ ወይም ቀጥረው በቀጥታ በሥራው የሚሳተፉበት የሥራ መስክ ነው:: መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ በይፋ የሚንቀሳቀስ የሥራ ዘርፍ ከመሆኑም በላይ ግለሰቦች የሥራ ዕድልን ለራስና ለቤተሰብ በመፍጠርና በአብዛኛው የዕለት ጉርስን ለማሟላት የሚከናወን የግል ወይም ቤተሰባዊ ድርጅትን ብቻ የሚያካትት ነው:: መደበኛ ያልሆነ የሥራ መስክ ወይም ድርጅት በአብዛኛው በዝቅተኛ ደረጃ ወይም የሥራ አደረጃጀት የተሠማሩ፣ በትንሽ የሥራ ማስኬጃና የተከፈለ /መነሻ/ ካፒታል የሚንቀሳቀሱ፣ ዝቅተኛ ወይም ምንም ቴክኖሎጂ የማይጠቀሙ፣ በአብዛኛው በጊዜያዊ የሥራ ቦታ የሚሠሩና መደበኛ በሆኑ የገንዘብ /የፋይናንስ/ ድርጅቶች ድጋፍ ወይም ብድር በማያስገኙ የሥራ መስኮች የተሠማሩትን ያጠቃልላል::

ስለሆነም መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት በሁሉም የሥራ መስኮች ማለትም በማምረት፣ በንግድ፣ በእርሻ፣ በትራንስፖርት፣ በሆቴሎችና በምግብ ቤቶች፣ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድንና በቁፋሮ እና በሌሎችም ስፋት ባለቸው የአገልግሎት ዘርፎች የተካተቱትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው::

መደበኛ ያልሆነው የሥራ ዘርፍ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በአጠቃላይ መልኩ የሚታወቅ ቢሆንም በሀገራችን ስለሥራ ዘርፉ ዝርዝር ሁኔታ ያለው መረጃ እጅግ ውስን ነው:: ስለዚህ የሥራ ዘርፉን ለማጠናከር መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በአስተማማኝ መንገድ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኗል:: ለሥራ ዘርፉ መጠናከር አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ለማውጣት በቅድሚያ የዘርፉን ልዩ ልዩ ባሕሪያት በዝርዝር ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

በተመሳሳይ መልኩም የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎችና የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ዘርፍም ለበርካታ በዘርፎቹ ለተሠማሩ ዜጎች የገቢ ምንጭ /መተዳደሪያ/ ከመሆናቸውም ባሻገር ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦና ድጋፍ እንደሚሰጡ ይታወቃል:: ይሁንና የእነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፎች ሁኔታ በግምት ላይ የተመሠረተ እሀዝ ከመጥቀስ ባሻገር ዝርዝር ስታቲስቲካዊ መረጃ የለም:: በመሆኑም የሥራ ዘርፎቹን ሁኔታ በዝርዝር ለማወቅ፣ ለማጠናከርና መወሰድ ያለባቸውን ዝርዝር የፖሊሲ

ውሳኔዎች ለመቅረፅ የዘርፎቹን ልዩ ልዩ ባሕሪያት በዝርዝር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማጥናትና በቂ ስታቲስቲክስ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው::

<u>የእነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ጥናቶች ዋና ዋና ዓላማዎች</u>

- በዘርፎቹ የተሠማራውን የሰው ኃይል ለማወቅ
- ዘርፎቹ ለሀገር ሀብት /GDP/ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለመገመገት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት
- እነዚህን የኢኮኖሚ ዘርፎች ለማጠናከር የሚያስፈልገውን ፖሊሲ /የፖሊሲ ለውጥ/ ለመቀየስ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት
- ዘርፎቹ ያሉበትን ሁኔታና የገጠሟቸውን ችግሮች ለማወቅና ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ናቸው::

### 6.2.4 <u>መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት</u>

በመሠረቱ ይህ ጥናት ከላይ በዝርዝር የቀረበውን መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍን ባሕርይ፣ አደረጃጀትና የሥራ ስምሪት ዓይነት በማጥናት የሌላ ታዳጊ አገሮችንና ዓለም አቀፍ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ልምድን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ መ/ቤት ጋር በመተባበር በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደ ጥናት ነው:: በአሁኑ ወቅት የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ተጠናቆ በመረጃው ላይ የእርማትና የኮድ አሠጣጥ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል:: መረጃዎችን በኮምፒዩተር የማቀነባበሩ ሥራ እንደተጠናቀቀ የጥናቱን ውጤት የሚያሳይ ሪፖርት ተዘጋጅቶ በ1989 በ3ኛው ሩብ ዓመት ለተጠቃሚዎች እንደሚሠራጭ ይጠበቃል::

### 6.2.5 <u>አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

ይህ ጥናት የሚሸፍናቸው በሞተር ኃይል ማለትም እንደ ኤሌክትሪክ፣ ውሃ ወይም በነፋስ የሚንቀሳቀሱ መሣሪያ በመጠቀም ቁጥራቸው ከአሥር በታች በሆኑ ሠራተኞች የሚንቀሳቀሱ ፋብሪካዎችን ነው:: በ1989 የሚካሄደው የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በመ/ቤታችን በስፋት ሲካሄድ ይህ የመጀመሪያው ሲሆን ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መጠይቆችና መመሪያዎች ዝግጅት እንደተጠናቀቀ በየደረጃው ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል:: በአሁኑ ወቅትም መረጃዎቹ በመስክ እየተሰበሰቡ ነው::

### 6.2.6 የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናት

ይህ ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በዚህ መልክ ሲጠና የመጀመሪያ በመሆኑና በጥናቱም የሚሸፈኑት ሁሉም የንግድ ዘርፎች ናቸው:: የዚህ ጥናት የዝግጅት ተግባር የተጠናቀቀ ሲሆን በሚቀጥለው የካቲት ወር የአሠልጣኞች ሥልጠና እንዲሁም ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዷል:: የመረጃ መሰብሰቡ ተግባርም ከየካቲት 20 እስከ መጋቢት ሦስተኛ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል::

### 6.2.7 የጎጆ/ዕደ ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

በዚህ ጥናት የሚሸፈኑ ማምረቻዎች በኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ ሳይጠቀሙ በእጅ ወይም በእግር የሚንቀሳቀስ መሣሪያ ተጠቅመው ወይም በሌላ መንገድ ምርት የሚያመርቱ የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎችን ነው:: ይህ ጥናት በገጠርና በከተማ የሚካሄድ ሲሆን የጥናቱም የዝግጅት ተግባራት ሥልጠናን ጨምሮ የተጠናቀቀ በመሆኑ መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት በመጋቢት ወር የመጨረሻ ሳምንት ውስጥ ነው::

### 6.2.8 ዓመታዊ ትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስታቲስቲካዊ ጥናት በባለሥልጣኑ መ/ቤት ከ30 ዓመታት በላይ በመደበኛነት በየዓመቱ እየተካሄደ ያለ ጥናት ነው:: ይህ ጥናት 10 እና ከ10 በላይ ሠራተኞችን በማሠማራት በሞተር ኃይል የሚሠሩ የማምረቻ ድርጅቶችን ብቻ የሚሸፍን በመሆኑ በዚህ ዘርፍ የመረጃ ክፍተት እንደነበረ ያመለክታል:: የተጠቀሰውን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት የአነስተኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ እንዲሁም የጎጆ ዕደ/ጥበብ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን የሚሸፍን ጥናት በያዝነው በጀት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲካሄድ በመደረጉ ችግሩን እንደሚያቃልል ታምኖበታል:: በመሆኑም የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በአጠቃላይ ለሀገር ሀብት የሚያበረክተውን ድርሻ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሟላ መልኩ በያዝነው በጀት ዓመት ከተካሄዱ ጥናቶች ለማግኘት እንደሚቻል ተገምቷል::

አገሪቱ ለምታካሂደው በእርሻ ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ዕድገት አቅጣጫ ለኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አውጭዎች በመነሻነት በማገልገል በኩል ከነዚህ ጥናቶች የሚሰበሰበው መረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እሙን ነው::

በ1989 በጀት ዓመት ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በሚያዝያ ወር ለማካሄድ ታቅዷል:: ከጥናቱ የሚገኙ መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው ወደ ዋናው

መ/ቤት እንደመጡ ተቀነባብረውና ተተንትነው በፕሮግራሙ መሠረት የጥናቱን ውጤት የሚያሳየው ሪፖርት ለተጠቃሚዎች ይሠራጫል።

### 6.2.9 የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት (Welfare Monitory Survey) ጥናት

በዚህ ጥናት የሚካተቱት:-

- የቤተሰቡ የትምህርት ሁኔታ
- የቤተሰቡ የጤና ሁኔታ
- ቤተሰቡ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች (amenities) እንደ ማገዶ፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የመብራት ዓይነት የመፀዳጃ ዓይነት ወዘተ... ያጠቃልላል።
- ስለቤተሰቡ ቋሚ ንብረቶች
- ስለአካባቢው የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና የአቅርቦት ሁኔታ
- የሕፃናት ክብደት፣ ቁመትና የጤና ሁኔታ ናቸው።

እነዚህንም ሁኔታዎች የሚያንፀባርቁ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን የጥናቱም ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የአገሪቱን የድህነት መስመር ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ለማግኘት

ለ. በአገሪቱ ውስጥ ለሚታየው የድህነት ሁኔታ መሠረታዊና ጠቋሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደፊት የሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ለመከታተልና ለማጥናት

ሐ. ድህነትን ለመቀነስና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እንዲቻል በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረና ዘላቂ መረጃ ለማቅረብ ነው።

ይህ ጥናት የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ክትትል ለማድረግ እንዲቻል ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት እንዲካሄድ በመወሰኑ ጥናቱም በያዝነው በጀት ዓመታት ለሁለተኛ ጊዜ ለማካሄድ በዕቅድ ተይዟል።

በዕቅዱም መሠረት ይኸው ጥናት በያዝነው ወር ውስጥ የጥናቱ የዝግጅት ተግባራት ተጀምሯል። በየደረጃው የሚሰጠው ሥልጠና በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቡ ተግባርም ጥር ወር መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃል ተብሎ ይበጠቃል። መረጃው ተሰብስቦ ከመስክ ተጠቃሎ እንደገባም ተቀነባብሮና ተተንትኖ በታቀደለት ፕሮግራም መሠረት ለተጠቃሚዎች ይሠራጫል።

### 6.2.10 <u>የኮንስትራክሽን የሥራ እንቅስቃሴ ጥናት</u>

የኮንስትራክሽን የሥራ እንቅስቃሴ ጥናት በመ/ቤታችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1988 የበጀት ዓመት የተሞከረ ሲሆን የዘርፉም የሥራ እንቅስቃሴ ልዩ ባሕርይ የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር የተለየ አድርጎት ነበር። የኮንስትራክሽን የሥራ እንቅስቃሴ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት በአንድ ቦታ የተወሰነ ብቻ አለመሆንና የሥራው እንቅስቃሴ ተለዋዋጭ መሆን እንዲሁም የብዙ ፕሮጀክቶች ከአንድ የበጀት ዓመት በላይ መቆየት ዓመታዊ ስታቲስቲካዊ መረጃ አሰባሰብ ተግባርን ውስብስብ አድርጎታል።

ከጥናቱ የሚገኘው መረጃ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለአገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድረሻ ለማስላት ያስችላል። ዘርፉ በተለይ ከሚጠይቀው የማቴሪያልና የሰው ኃይል ፍላጎት አንፃር ሲታይ የኮንስትራክሽን ሥራ በአንድ አገር የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት የታወቀ በመሆኑ የዘርፉን እንቅስቃሴ ስታቲስቲካዊ መረጃ ማግኘት ከፍተኛ ጠቃሚነት እንዳለው ይታወቃል። ምክንያቱም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው በምን ዓይነት እርምጃ እየሄደ መሆኑን የሚያሣይ ጠቋሚ መሣሪያ በመሆኑ ነው።

ባለፈው በጀት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ በናሙና በተመረጡ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ላይ የተካሄደው የዚሁ ክፊለ ኢኮኖሚ ጥናት ውጤት ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን፣ በያዝነው በጀት ዓመትም የዚህን ክፍለ ኢኮኖሚ ጥናት ሰፋ ባለመልኩ ለማጥናት ታቅዷል። ጥናቱም ግንቦት ወር እንደሚካሄድ ይጠበቃል።

### 6.2.11 <u>የእንሰት ጥናት</u>

እንሰት በአገራችን በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ክፍል በሚገኙ የአስተዳደር ክልሎች የሚበቅልና በርካታ ሕዝቦች በምግብነት የሚጠቀሙበት ሰብል ነው። ይኸው ሰብል ከቃጫ ምርቱና ከምግብ ሰብልነቱ በተጨማሪ ድርቅንና በሽታን የመቋቋም ባሕርይ እንዳለው በጥናት ተረጋግጧል። በነዚህና በሌሎች የሰብሉ ባሕሪያት አገራችን በምግብ ሰብል ምርት ራሷን ለመቻል በምታደርገው ከፍተኛ ጥረት ጉልህ እገዛ እንደሚያደርግ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል።

በመሆኑም ሰብሉን በተመለከተ አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች መኖር በአጠቃላይ የግብርናውን ክፊለ ኢኮኖሚ የበለጠ ምርታማ እንዲሆን የሚደረገውን ጥረት የተሟላ ያደርገዋል። ስለሆነም ከጥናቱ የሚገኙ መረጃዎች:-

- በእንሰት ሰብል የተያዘውን የመሬት ስፋትና የሚገኘውን የምርት መጠን የሚያሳይ መረጃ ያስገኛል።

- የእንስት ሰብል በእንስት አብቃይ ክልሎች የሚያደርገውን ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎችን ያስገኛል።

ጥናቱንም በያዝነው በጀት ዓመት በሚያዝያና ግንቦት ወር ውስጥ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የዝግጅት ሥራዎች በመገባደድ ላይ ይገኛሉ።

### 6.2.12 ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔትን ለማዘጋጀት በየዓመቱ ከተለያዩ መ/ቤቶች እንደ ጤና ጥበቃ፣ ትምህርት ሚ/ር፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ...ወዘተ. ከአስተዳደር መዛግብት መረጃዎችን በማሰባሰብ አጠናቅሮ በተፈለገው ዓይነት በመጽሔቱ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል። በተጨማሪም በባለሥልጣኑ መ/ቤት ውስጥ ከሚካሄዱ ጥናቶችና ቆጠራዎች የሚገኙትን መረጃዎች ጠቅለል ባለመልኩ በመጽሔቱ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል።

ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ውስጥ ከሚካተቱት በርካታ መረጃዎች መሃል ዋና ዋናዎቹ፡-

- ሥነ ሕዝብ መረጃዎች
- ዓመታዊ የሀገር ሀብት ውጤት መረጃዎች
- የመንግሥት ገንዘብ/ፐብሊክ ፋይናንስ/ መረጃዎች
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች
- የመድን /ኢንሹራንስ/ መረጃዎች
- ጤናና ትምህርት መረጃዎች ...ወዘተ. ናቸው።
- ሕግና ደንብ እና ስፖርት
- የግብርና ነክ መረጃዎች
- የማዕድን ምርት መረጃዎች
- ማምረቻና ኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃዎች
- ስለ ሕንፃዎች ሥራ

7. <u>የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት በንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ጊዜ የነበረው የሰው ኃይል ብዛት ከ20 የማይበልጥ ነበር። ይሁን እንጂ መሥሪያ ቤቱ ከተጣለበት ኃላፊነትና ተግባር መካከል አንዱ ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝ መረጃ መሰብሰብ ፣ መተንተንና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት በመሆኑ መሥሪያ ቤቱ የሰው ኃይሉ በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ከዓመት ዓመት ለማሣደግ ተከታታይ ጥረት አድርጓል።

ይህንንም ለማድረግ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አጠቃላይ ግንባታ ከሰው ሃይል ግንባታ ጋር በቀጥታ የተቆራኘ በመሆኑ የሚፈለገው የሰው ኃይል ዓይነትና በቅጥር እንደዚሁም ያሉትን ሠራተኞች ደግሞ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠና እንዲከታተሉ በማድረግ የሰው ኃይሉን ለማሳደግ ተችሏል።

ለግንዛቤ እንዲረዳም በታህሣሥ 30 ቀን 1989 ላይ የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የነበረው የሰው ኃይል 416 ቋሚ እና 1,631 የኮንትራት በድምሩ 2,047 ሠራተኞች ይሆናሉ። የቋሚ ሠራተኞቹ ብዛት በሙያ ሲተነተን 114 ፕሮፌሽናሎች፣ 154 መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ 148 ደግሞ የአስተዳደር፣ የጽሕፈት እና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። እንደዚሁም የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በጾታ ሲለይ 306 ወንዶች /73.6 በመቶ/ሲሆኑ 110 ደግሞ ሴቶች /26.4 በመቶ/ ናቸው።

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የሰው ኃይል ሁኔታ ከ1984 እስከ 1989 ድረስ

| በጀት ዓመት | የሠራተኛ የቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|
| | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1984 | 425 | 1183 | 1608 |
| 1985 | 502 | 1103 | 1605 |
| 1986 | 488 | 1146 | 1634 |
| 1987 | 493 | 1206 | 1699 |
| 1988 | 470 | 1685 | 2155 |
| 1989 | 416 | 1631 | 2047 |

## 8. የመ/ቤቱ የፋይናንስ አጠቃቀም ሁኔታ

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የራሱ በጀት ተመድቦለት መንቀሳቀስ የጀመረው ከ1955 ዓ.ም ወዲህ ነው። በዚህ ወቅት የመሥሪያ ቤቱ በጀት ከብር 200,000 የማይበልጥ ነበር።

ይሁን እንጂ መሥሪያ ቤቱ የሚያከናውናቸው ጥናቶች ከዓመት ዓመት እየጨመሩ በመምጣታቸው እንደዚሁም ጥናቶቹን የሚያካሂደው የሰው ኃይል በብዛትም በጥራትም በማደጉና ሥራው በዘመናዊ መሣሪያዎች (በኮምፒዉተር፣ በሕትመት መሣሪያዎችና በመስክ ተሽከርካሪዎች ...ወዘተ) በመታገዝ መከናወን ስላለበት በጀቱ በዚሁ መጠን ሊያድግ ችሏል።

ከላይ የተጠቀሱትን ለማሟላት መንግሥት በካፒታል በጀት ምደባ ረገድ እስከ 1987 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተቻለውን ያህል ድጋፍ ያደረገ ቢሆን ለ1988 እና 1989 በጀት ዓመት ለጥናቶች ማስፈፀሚያ በመንግሥት የተፈቀደው ካፒታል በጀት ግን አነስተኛ ነው። በመሆኑም በ1988 እና1989 በተመደበ በጀት በተቀናጀ ቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም ሊጠኑ የታቀዱ ጥናቶች ቀደም ሲል በነበረው የጥናት ሽፋን ደረጃ ማካሄድ ባለመቻሉ የናሙናውን መጠን ዝቅ ማድረግ የግድ ሆኗል። ስለዚህ ቀደም ሲል የጥናቶች ሪፖርት በዛን ደረጃ ሊቀርብ የነበረዉ በበጀት እጥረት

ምክንያት ለሶስት ትላልቅ ክልሎች በስተቀር ሪፖርቶቹ በክልል ደረጃ ብቻ እንዲቀርቡ ሁኔታዉ አስገድዷል። ለሶስቱ ትላልቅ ክልሎችም (ኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ሕዝቦች) ቢሆን ከክልል በታች በዞኖች ስብስብ (Group of Zones) ደረጃ ብቻ ነዉ የጥናቶቹን ሪፖርቶች ማቅረብ የተቻለዉ።

በሌላ በኩል ከውጭ እርዳታ ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ዕርዳታ በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ማግኘት አዳጋች እየሆነ ነው። ይህም የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ለድርጅታዊ አቅም ግንባታ ብሎም ለሀገር አቀፍ የስታቲስቲክስ መረጃዎች መሰብሰብ፣ ማቀነባበር፣ መተንተንና ብሎም የማሠራጨት ተግባር መጎልበት በሚያደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያደርስ ግልጽ ነዉ።

ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ በመንግሥት የተፈቀደው መደበኛና ካፒታል በጀት መጠን የስድስት ዓመት የበጀት ዝርዝር በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በመንግሥት የተፈቀደ መደበኛና ካፒታል በጀት

(በሚሊዮን ብር)

| የበጀት ዓይነት | የበጀት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1984 | 1985 | 1986 | 1987 | 1988 | 1989 |
| መደበኛ በጀት | 3.2 | 16.7 | 4.0 | 4.1 | 3.8 | 4.0 |
| ካፒታል በጀት | 5.2 | 10.0 | 15.0 | 72.1 | 8.2 | 21.8 |
| ድምር | 8.4 | 26.7 | 19.0 | 76.2 | 12.0 | 25.8 |

መግለጫ

1. የ1985 መደበኛ በጀት መጠን ከፍ ያለዉ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ካርታ ሥራ ማስፈጸሚያ 13.2 ሚሊዮን ብር አስቸኳይ በጀት በመንግሥት በመፈቀዱ ነዉ።
2. የ1987 ካፒታል በጀት መጠን ከፍ ያለዉ በሕዝብና ቤት ቆጠራ ምክንያት ነዉ።
3. የ1989 የካፒታል በጀት መጠን ከፍ ያለዉ በአፋርና በሶማሌ ብሄራዊ ክልሎች ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማካሄድ ተጨማሪ በጀት በመመደቡ ነዉ።

## 9. በልምድ ልውውጥ የስታቲስቲክስ ሥራን ለማሻሻል የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ጥናቶችን በማካሄድ የራሱ የሆነ በርካታ ልምዶችን አካብቷል። ከዚህ በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ከሚያዘጋጀው ሴሚናሮችና ወርክሾፖች ላይ ከሚሣተፉ ባለሙያዎች በሚቀርቡ ገንቢ አስተያየቶች /ትችቶች ሥራውን የበለጠ ለማሻሻል ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሌሎች ባለሙያዎች በአሁጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ሰሚናሮችና ወርክሾፖች ላይ በመሣተፍ የመሥሪያ ቤቱ አሰራር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መጥቷል።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው መሥሪያ ቤቱ የሚያካሄዳቸው ጥናቶች ከዓመት ዓመት እያደጉ በመምጣታቸው እንደዚሁም ለመጀመሪያ ጊዜ በግንቦት ወር 1976 የተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ በአፍሪካ አህጉር በጥራት ከተካሄዱት ቆጠራዎች እንደ አንዱ በመገመቱ ሌሎች ሀገሮች የስታቲስቲክስ ጥናቶችንና የሕዝብና ቤት ቆጠራ አሠራርን በተመለከተ ልምድ ለመቅሰም ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሕዝብና ቤት ቆጠራን አሠራር በተመለከተ ልምድ የገበዩት ከናይጄሪያ፣ ከሴራሊዮን፣ ከየመን ሪፐብሊክና ከሞዛምቢክ የመጡ ናቸው።

አሁንም ቢሆን የስታቲስቲክስ ሥራ በየዘመኑ ከሚፈጠረው ሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ጋር አብሮ የሚያድግ በመሆኑ መሥሪያ ቤቱ እነዚህን አዳዲስ አሠራሮችን በመከታተል በሥራ ለመተርጎም ክትትል እያደረገ ነው።

## 10. የመሥሪያ ቤቱ ሥራዎችን ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸዉ መሣሪያዎች ሁኔታ

መሥሪያ ቤቱን በተለያዩ ፋሲሊቲዎች የተሟላ ለማድረግ ተከታታይ ጥረቶች ተደርገዋል። በተደረገው ጥረትም ከውጭ ዕርዳታ በርካታ ቋሚ እቃዎችና መሣሪያዎች ተገኝተዉ ለመ/ቤቱ አገልግሎት እየዋሉ ነዉ። በዚህም መሠረት

በእርዳታ በተገኙ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ተጠናከረዉ የሚገኙት ክፍሎች የመስክ ሥራ አገልግሎት፣ የመረጃ ትንብር፣ ካርቶግራፊንና የሕትመት ክፍሎች ናቸዉ።

11. ያጋጠሙ ችግሮች

በሂደት ያጋጠሙ ችግሮች የተለያዩና ብዛት ያላቸው ቢሆኑም የመ/ቤቱ ማኔጅመንት በሚወስዳቸው እርምጃዎችና ከአቅም በላይ የሆኑትን ለበላይ አካል የውሣኔ አስተያየት ጭምር በማቅረብ የመፍትሄ እርምጃ በማስወሰድ መ/ቤቱ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት ከሞላ ጎደል ሲወጣ ቆይቷል። ቀደም ሲል የነበሩትን ሁኔታዎች በመተው በአሁኑ ወቅት ብቻ ትኩረትና ውሣኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ማተኮሩ ይበቃል ተብሎ ታምኖበታል። ይኸውም፣

ሀ. ከኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት መቋቋም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የመዋቅር ለውጥ መ/ቤታችንን አስመልክቶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ባለመኖሩና እንደዚሁም በመንግሥት መመሪያ የመዋቅር ለውጥ ባልተደረገባቸው መ/ቤቶች ቅጥርና እድገት በመታገዱ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮች ተፈጥረዋል። ይህም ባሉት ከፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ በቅጥርና በደረጃ እድገት መመደብ ባለመቻሉ በአፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል።

ለ. የስታቲስቲክስ መረጃ ተጠቃሚዎች በተቻለ መጠን የጥናቶች ሪፖርት ደረጃ በአነስተኛው የአስተዳደር ክፍፍል ማለትም በወረዳ ወይም በዞን ደረጃ ቢሆንላቸው ይመርጣሉ። ሆኖም በዚህ ደረጃ ውጤቱን ለማዘጋጀት የባለሥልጣኑ መ/ቤት የበጀት እጥረት /ቅንሣ አጋጥሞታል። ስለዚህ የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማሟላትና እንደዚሁም የተሟላና አጥጋቢ ውጤት ለማስገኘት የበጀት መጠን ታስቦበት እንዲፈቀድ ያስፈልጋል።

ሐ. በመስክ የሚሰበሰበው መረጃ ጥራት የሚወሰነው የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሲደረግበት በመሆኑና ለዚህም በብዛትም ሆነ በጥራት የመስክ ተሽከርካሪ

መኪናዎች ተጓልተው መገኘት ወሣኝነት አለው። ሆኖም መ/ቤቱ ተደም ሲል ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በእርዳታ ከውጪ ያገኛቸው መኪናዎች ብቻ ሲሆን እነዚህም መኪናዎች ከአገልግሉት ብዛት የተነሳ የጥገና ወጪአቸው ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ የሚሰጡት አገልግሎትም ውስን ሆኖአል። ስለዚህ ለአሁኑም ሆነ ወደፊት በእቅድ ለተያዙት ጥናቶች ማስፈፀሚያ በብዛትም ሆነ በጥራት ብቁ የሆኑ መኪናዎች የሚገኙበት መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

12. <u>የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የወደፊት የሥራ እቅድ</u>

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በ1986 ዓ.ም የአምስት ዓመት /ከ1987 እስከ 1991/ የጥናት እቅዶች አዘጋጅቶ ለፕላንና ኢኮኖሚ ልማት/ አሁን የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር/ አቅርቧል። እነዚህም ጥናቶች ለቀሩት ሁለት ዓመታት የሚከተሉት ናቸዉ፣

ሀ. በ1990 በጀት ዓመት፣

- የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት /በገጠር/
- የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የጤናና አመጋገብ ጥናት /በገጠርና በከተማ/
- የሻይታል ስታቲስቲክስ ጥናት /በገጠርና በከተማ/
- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት /በገጠርና በከተማ/
- የዋጋዎች ጥናት /በከተማ/

ለ. በ1991 በጀት ዓመት፣

- የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት፣ /በገጠር/

- የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናት /በገጠር/

- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት /በገጠርና በከተማ/

- የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት /በገጠርና በከተማ/

- የሰዉ ኃይል ጥናት /በገጠርና በከተማ/

- የዋጋዎች ጥናት በከተማ ናቸዉ።

ከላይ ከተዘረዘሩትና በዕቅድ ከተያዙት ጥናቶች በተጨማሪ መንግሥት እንዲጠኑ የሚፈልጋቸውን ጥናቶችንም በማጥናት ላይ ነው። ለመጥቀስ ያህል የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት በ1987 እንዲጠና መንግሥት በጠየቀው መሠረት በመጠናት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የግብርና ቆጠራ ጥናት እንዲካሄድ መንግሥት መመሪያ በሰጠዉ መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ ፕሮጀክት ዶክሜንት ተዘጋጅቶ እንዲፈቀድ ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ቀርቧል።